**ዙሮ ፡ ዕያዩ ፡ ጉዞ ፤**

አይ ፡ እናታችን!!
አቤት ፡ በይ ፡ እስቲ ፡ ጳጳሱን ፣ አቡኑን ፣ ዲያቆኑን ፣
ምዕመኑን ፣ ደብተራውን ፣ ስደተኛ ፡ ዕረፍት ፡ የለሹን ፣
በዓለም ፡ አቀፍ ፡ መረብ ፡ ዜና ፡ ዘጋቢውን ።
ወይ ፡ ልጆቸ!!
በእርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ንትርክ ፡ ተጐድቸ ፣
እስቲ ፡ እናንተም ፡ እያንዳንዳችሁ ፣
አብሮ ፡ ለመኖር ፡ ተስማምታችሁ ፣
ድርሻየ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፣
ተጠያየቁ ፡ እባካችሁ ።
አንገትሽን ፡ አቁስለው ፡ ዳባ ፡ አስታጥቀውሽ ፣
ሹርባሽን ፡ ቆርጠው ፡ ፍቀው ፡ ላጭተውሽ ፣
ጠላትና ፡ ወዳጅ ፡ ለልጅሽ ፡ ፈጥረሽ ፣
ምልምል ፡ አድርገሽው ፡ ዋና ፡ ጸሐፊሽ ፣
ቤትሽን ፡ አጥረውት ፡ በቁምሽ ፡ ታሥረሽ ፣
ጸሎትሽን ፡ ጨርሰሽ ፡ እስቲከፈት ፡ በርሽ ፣
አንገትሽም ፡ እስቲድን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይማርሽ ።
ዙሮ ፡ ዕያዩ ፡ ጉዞ ፡ ተጠባብቀን ፡ መክረን ፤
የእሳት ፡ ልጅ ፡ አመዱ ፡ ተነሣና ፡ ብነን ፤
ጠላትን ፡ ዐውረህ ፡ አገር ፣ ወገን ፡ አድን ።

ቆይቸ ፡ ነበረ ፡ እየተገላመጥኩ ፣
በልሣነ ፡ ግዕዝ ፡ በደስታ ፡ ዓለማየሁ ፣
ዓይኔን ፡ አላመንኩት ፡ ሐሣቤን ፡ አልገታሁ ፣
በነፃነት ፡ ኖሬ ፡ ችግር ፡ ስላልቀመስሁ ።



ለካ ፡ እንደዚህ ፡ ኖሯል ፡ ቁልል ፡ ምርት ፡ ነፃነት ፣
ሳልገነዘበው ፡ አድጌ ፡ ሳልሸምት ፣
የግዕዝ ፡ አዝመራ ፡ የማያልቅ ፡ ቢዝቁት ፣
ቀድሞ ፡ ተበትኖ ፡ ተናኝቶ ፡ በዓለማት ።
ዙሮ ፡ ዕያዩ ፡ ጉዞ ፡ ተጠባብቀን ፡ መክረን ፣
የእሳት ፡ ልጅ ፡ አመዱ ፡ ተነሣና ፡ ብነን ፣
ጠላትን ፡ ዐውረህ ፡ አገር ፣ ወገን ፡ አድን ።

የቋንቋ ፡ እናት ፡ አባት ፡ እያለ ፡ ከቤቴ ፣
ወይ ፡ አለማወቄ! እንዲያ ፡ መሞኘቴ ፤
ሳወራ ፡ ከርሜ ፡ ይመስላል ፡ በማለት ፣
የቅድም ፡ አያቴ ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ።
መልሰው ፡ ከልሰው ፡ የመገቡንን ፤
የእናታችን ፡ ታሪክ ፡ የዘረፉትን ፣
እንግዛችሁ ፡ ብለው ፡ ለሚያንገራግሩን ፣
እሷንም ፡ አቋሸው ፡ ያቃለሏትን ፣
ደምመላሽ ፡ መጣና ፡ ከእንቅልፍ ፡ ቀስቅሶን ፣
በኅብረት ፡ ተነሡ ፡ ተዘጋጁ ፡ አለን ፣
ጦር ፡ ጋሻችን ፡ ይዘን ፡ ጠላት ፡ ልናድን ፣
ለአገርና ፡ ወገን ፡ መከታ ፡ ልንሆን ።
ዙሮ ፡ ዕያዩ ፡ ጉዞ ፡ ተጠባብቀን ፡ መክረን ፣
የእሳት ፡ ልጅ ፡ አመዱ ፡ ተነሣና ፡ ብነን ፣
ጠላትን ፡ ዐውረህ ፡ አገር ፣ ወገን ፡ አድን ።

ዕንቅፋት ፡ ብዙ ፡ እርምጃ ፡ ቢሆንም ፣
ፊት ፡ ኋላ ፡ እየታየ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ቢዘገም ፣
ተባብሮ ፡ ሲነሡ ፡ የሚቸግር ፡ የለም ።

እማማ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክብርት ፡ አናታችን ፣
ታሪክሽን ፡ ሰርቀው ፡ ያበላሹብንን ፣
የፈረንጅን ፡ ቅጥፈት ፡ አብራርቶ ፡ እሚያስረዳን ፣
በጕኑ ፡ አሰልፎ ፡ ደራሲ ፡ አጋሩን ፣
ለዋቢ ፡ የሚሆ ፡ መጻጽፍ ፡ ለሰጡን ፣
የትውልድ ፡ ጌጦችሽ ፡ ውድ ፡ ልጆችሽን ፣
ግዕዝ ፣ አማርኛ ፡ ጠባቂዎችሽን ፣
ነባር ፡ መገናኛ ፡ ላንድነታችን ፣
እግዚአብሔር ፡ አምላክሽ ፡ እንዲያቆይልን ፣
አንችንም ፡ በሰላም ፡ ሊጠብቅልን ፣
በልባዊ ፡ አንድነት ፡ እንመኛለን ።
ዙሮ ፡ ዕያዩ ፡ ጉዞ ፡ ተጠባብቀን ፡ መክረን ፣
የእሳት ፡ ልጅ ፡ አመዱ ፡ ተነሣና ፡ ብነን ፣
ጠላትን ፡ ዐውረህ ፡ አገር ፤ ወገን ፡ አድን ።

ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ እርምጃ ፡ አስከፊ ፡ መስሏችሁ ፣
እንዳትታለሉ ፡ ጠይቁ ፡ እባካችሁ ፣
በሩን ፡ ክፍት ፡ አድርጐ ፡ እየጠበቃችሁ ፣
ግቡ ፡ ተቀመጡ ፡ ዛሬስ ፡ ምን ፡ አሻችሁ ፣
በማለት ፡ ከልቡ ፡ ሊያስተናግዳችሁ ፣
ሐዋርያው ፡ ጀግና ፡ ቆራጥ ፡ ወንድማችሁ ፣
ልበ ፡ ሙሉ ፡ አስተዋይ ፡ ደፋሩ ፡ አለኝታችሁ ፣
ኢትዮጵያዊው ፡ ምሁር ፡ ቋሚ ፡ ደብተራችሁ ፣
አርቆ ፡ የሚያሥብ ፡ መካር ፡ ሳለላችሁ ፣
የእማማን ፡ ቃል ፡ ከትቦ ፡ ላቀረበላችሁ ፣
መጽሐፍ ፡ ቅዱሱንም ፡ አንብቡ ፡ አደራችሁ!!
ደግሞም ፡ ወገኖቸ ፡ ሌላ ፡ የሚበጅ ፣



ይኸ ፡ ሐዋርያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጅ ፣
የእኛ ፡ ወንደማችን ፡ ደጋግሞ ፡ እንዲያዘጋጅ ፤
አይዞህ ፡ እንበለው ፡ ይንቃ ፡ ሕሊናችን ፣
የምዕራቡን ፡ ተንኮል ፡ ፍቀን ፡ ከአዕመሯችን ፣
የታሪክ ፡ አተላ ፡ መሆኑን ፡ መዝግበን ፣
ያለፈው ፡ ይበቃል ፡ ዳግመኛ ፡ አያሞኘን ።
እንበርታም ፡ በሉ ፡ ካሰነበተን ፣
ዙሮ ፡ ዕያዩ ፡ ጉዞ ፡ መጥፎ ፡ አይምሰለን ፣
ይረዳናል ፡ እና ፡ ለማመዛዘን ፣
መውጫና ፡ መግቢያችን ፡ መድረሻችንን ፣
አዝግመን ፡ ለመጠር ፡ ኢትዮጵያ ፡ እማማን ።
ዙሮ ፡ ዕያዩ ፡ ጉዞ ፡ ተጠባብቀን ፡ መክረን ፣
የእሳት ፡ ልጅ ፡ አመዱ ፡ ተነሣና ፡ ብነን ፣
ጠላትን ፡ ዐውረህ ፡ አገር ፣ ወገን ፡ አድን ።

ሰላምን ፡ አወርድልን ። አሜን ።

የካቲት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፱ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ።